King County

# የኮቪድ -19 ክትባት

## ማጠቃለያ

የኮቪድ-19 ክትባት ለድንገተኛ ግዜ ጥቅም በምግብና መድኃኒት አስተዳደር (FDA) ጸድቋል። የስያትልና ኪንግ ካዉንቲ ሕዝብ ጤና ከዋንሸግተን ስቴት ጤና ክፍል ጋር በመተባበር በክትባት ስርጭት ዕቅዶች ላይ እየሠራ ነዉ።

- የመጀመሪያ የክትባት አቅርቦት የተወሰነ በመሆኑ፤ መጀመሪያ ከፍተኛ ስጋት ላለባቸዉ የተወሰኑ ቡድኖች እንደ ጤና እንክብካቤ ዉስጥ ያሉ ሠራተኞች ና በነርሲንግ ቤቶች ና ሌሎች የረጅም ግዜ እንክብካቤ መስጫ ተቋማት ዉስጥ ላሉ ሰዎች ይሰጣል።
- የኮቪድ-19 ክትባት እስከ 2021 ድረስ በሰፊዉ አይቀርብም። በመጨረሻ ክትባቱ በተመከሩ ቡድኖች ላለ ሰዉ ሁሉ ይቀርባል።
- የክትባት ደህንነት ቅድሚያ ይሰጠዋል። ሁሉም የኮቪድ-19 ክትባቶች ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት በጠንካራና እርምጃ-ብዙ ሙከራ፣ ግምገማ እንዲሁም የማጽደቅ ሂደት ማለፍ አለባቸዉ። የFDA የደህንነትና ዉጤታማነት ደረጃዎች ሲያልፉ ብቻ ነዉ ፈቃድ ማግኘት የሚችሉት። ክትባቶቹ ኣንዴ ከተሰጡ በኋላም የደህንነት ቁጥጥር ይካሄድባቸዋል።

## የመጀመሪያ ኮቪድ-19 ክትባት ስርጭት ዉስን ነዉ እና አሰጣጡ ቅደም ተከተል ያስፈልገዋል

በመጨረሻ ክትባት የሚፈልግ ሁሉ ያገኛል። ሆኖም ግን ክትባቱ መጀመሪያ ሲቀርብ የአቅርቦት ገደብ አለ። ክትባቱ በመጀመሪያ የሚሰጠዉ በኮቪድ-19 የመያዝ ከፍተኛ ስጋት ላለባቸዉ የተወሰኑ ሰዎች ወይንም በኮቪድ-19 ከተያዙ ሌላ ከባድ የጤና ሁኔታ ያለባቸዉ እንደ ጤና እንክብካቤ ሠራተኞች፣ ነርሲንግ ሆም ወይንም እርዳታ-ሰጭ (ኣሲስትድ ሊቪንግ) ተቋማት ውስጥ የሚኖሩ አዋቂዎች፣ እንዲሁም ሌሎች ወሳኝ ሠራተኞች ይሆናል።

## ማነዉ አሁን መከተብ የሚችለዉ

የዋሸንግተን ስቴት ጤና ዲፓርትመንት (DOH) ለኛ ስቴት የክትባቱን ስርጭት ይወስናል። አሁን የስርጭቱ የመጀመሪያ ዙር "ዙር 1a" የሚባለዉ ላይ ነን (ድህረ ገጽ በእንግልዝኛ ብቻ ነዉ)። በዙር 1a ወቅት ከፍተኛ ስጋት ባለባቸው የጤና እንክብካቤ ቦታዎች ያሉ ሠራተኞችና የረጅም ግዜ እንክብካቤ መስጫ ተቋማት (እንደ ነርሲንግ ቤቶች፣ ድጋፍ ተሰጥቶ የሚኖርባቸዉ ቤቶች፣ የአዋቂዎች መንከባከቢያ ቤቶች) ዉስጥ ያሉ ሰዎች ክትባቱ ይሰጣል።

DOH ለበርካታ ሆስፒታሎች፣ መድኃኒት ቤቶች፣ እና ክትባቱን ለመቀበል ለተመዘገቡ የጤና ስርዓቶች ክትባቱን አቅርቧል። DOH እና የስያትልና ኪንግ ካዉንቲ ማህበረሰብ ጤና የክትባት መስጫ ጣቢያዎችን እና የከተባቱን ተደራሽነት ለመጨመር ከብዙ ሸሪኮች ጋር እየሰሩ ነዉ።

ብዙ የረጅም ግዜ እንክብካቤ መስጫ ተቋማት ነዋሪዎች እና ሠራተኞች ከመድኃኒት ቤቶች ባለዉ ሽርክና ክትባቶችን ያገኛሉ።

የዋሸንግተን ስቴት ጤና ዲፓርትመንት (DOH) ሰዎች በዙር 1a ክትባት ለማግኘት ብቁ መሆናቸዉን እንዲያዉቁ ለመርዳት የኦንላይን ግለ ዳሰሳ ያዙር መፈለጊያ (ድህረ ገጽ በእንግልዝኛ ብቻ ነዉ) መሣሪያ እየሰራ ነዉ። የዙር መፈለጊያ በተጨማሪ የሚያቀርበዉ፡

- ክትባት ጣቢያ ላይ ማሳየት የሚቻል የብቁነት ማረጋገጫ።
- ለክትባት ክፍት የሆኑ ጣቢያዎች ዝርዝር ማስፈንጠርያ።

የዙር መፈለጊያ በአሁኑ ሰዓት የሚሸፍነዉ ለዙር 1a ብቁ የሆኑትን ብቻ ነዉ ግን ለሌሎች ቅድሚያ የሚሰጣቸዉ ቡድኖች ስቴቱ ወደ አዲስ የክትባት ስርጭት ዙሮች ስገዝ ክፍት ይሆናሉ።

## የክትባት ወጪ

- የኮቪድ ክትባት በሜዲኬር፣ ሜዲኬድ ና በርካታ የግል ኢንሹራንስ ይሸፈናል፤ የክትባቱ ወጪ ኢንሹራንስ ለሌላቸዉ ሰዎችም ይሸፈናል። በኢንሹራንስ ዕቅድዎ ወይንም ክትባት ለማግኘት የሚያዩት ሓኪም መሰረት የወጪ መጋራት ክፍያ ወይንም የቢሮ ጉብኝት ክፍያ ሊኖር ይችላል።
- የክትባት ኣቅርቦት ሲኖር፡ የሕዝብ ጤና በአነስተኛ ወጪ ወይንም በነጻ ክትባት የማግኘት ዕድል በሚሰጡ ክሊኒኮች እያቀደ ነዉ።

## የክትባት ደህንነት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነዉ

የኮቪድ-19 ክትባቶች ብዙ ሺ የጥናት ተሳታፊዎች ክትባት የሚቀበሉበት ጠንካራና/ጥብቅ በሆኑ የክሊኒክ ሙከራዎች ማለፍ አለባቸዉ። የምግብና መድኃኒት አስተዳደር (FDA) የያንዳንዱን ክትባት ደህንነትና ዉጤታማነት ለመወሰን ከነዚህ ጥናቶች የሚገኙትን መረጃዎች ይገመግማል። FDA በገለልተኛ ሳይንቲስቶችና ባለሙያዎች አማካሪ ቡድን ትንተናና ምክረ ሃሳቦች ላይ ይመረኮዛል፤ Vaccines and Related Biological Products Advisory Committee (VRBPAC)። የ VRBPAC ስብሰባዎች ለህዝብ ክፍት ናቸዉ።

ክትባቱ የ FDA ደህንነትና ዉጤታማነት መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ፡ FDA ክትባቱ አሜሪካ ዉስጥ ጥቅም ላይ እንዲዉል ሁኔታዎች ማመቻቸት ይችላል።

FDA ኣም ከወሰደ በኋላ ሁለተኛ ገለልተኛ የሆነ ሁለተኛ የክትባት ባለሙያዎች አማካሪ አካል፤ የኣሜሪካ Advisory Committee on Immunization Practices (ACIP), የክትባቱን ደህንነትና ዉጤታማነት መረጃ ያዩና ሊሲዲሲ ስለ ክትባቱ ምክረ ሃሳብ ይሰጣል።

**የክትባት የደህንነት ቁጥጥር:**

ክትባቱ ጥቅም ላይ እንዲዉል ከተፈቀደ በኋላ፡ ሊከሰቱ የሚችሉ የጎንዮሽ ጉዳት ለማየት በርካታ የደህንነት ቁጥጥር ስርዓቶች ይኖራሉያልታሰበ ከባድ የጎንዮሽ ጉዳት ከታየ ባለሙያዎች በተቻለ ፍጥነት እዉነተኛ የደህንነት ስጋት መሆኑን ለማረጋገጥ ይሠራሉ። የክሊኒክ ሙከራዎቹ ካለቁ በኋላ እንኳን ይህ እንደ ተከታታይ የደህንነት ግምገማ ሆኖ ያገለግላል። ለኮቪድ-19 ክትባት፡ ደህንነታቸውን በወቀቱ ለመገምገም እና የኮቪድ ክትባቱ ዓቅም እስከፈቀደው መጠን ደህንነቱን የተጠበቀ እንደሆነ ለማረጋገጥ ሲዲሲ እና FDA የደህንነት መቆጣጠርያ ስርዓትን ኣስፍተዋል።

- ለተጨማሪ መረጃ: የኮቪድ-19 ደህንነት በአሜሪካ ዉስጥ ማረጋገጥ CDC

**ፈቃድ ያላሸዉና የሰለጠኑ የጤና ባለሙያዎች ብቻ ናቸዉ ክትባቶች ሊሰጡ የሚችሉት**

ክትባት ለመስጠት ፈቃድ ያላቸውና የሰለጠኑ ግለሰቦች ብቻ ናቸዉ ክትባት መስጠት የሚችሉት። አንዴ ክትባቱ ለጠቅላላ ማህበረሰብ በሰፊዉ መቅረብ ከጀመረ ብዙ ዓይነት የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ክትባት ይሰጣሉ። እነዚህ አቅራቢዎች በክሊኒኮች ና ሆስፒታሎች እንዲሁም ተንቀሳቃሽ ወይም በየግዜው ህብረተሰቡ ውስጥ ብቅ የሚሉ ኩነቶች ላይ ክትባቶች ሊሰጡ ይችላሉ።

## ሁሉንም የኮቪድ-19 ጥንቃቄዎችን መቀጠል ጠቃሚ ነዉ +

- ደህንነቱ የተጠበቀ ና ዉጤታማ የኮቪድ-19 ክትባት ትልቅ እምርታ ነዉ። ኘ ክትባት ብቻዉን ወረርሽኙን አሁኑኑ አያስቆምም።
- ክትባቱ ከቀረበ በኋላ እንኳን ወረርሽኙን ማስቆም ሁሉም ራሳቸዉንና ሌሎችን ለመከላከል በአሁኑ ያሉትን ሁሉንም መመሪያዎች መከተልን ይጠይቃል ምንም እንኳን ተከትቦም ቢሆን። ይህም ማስክ መልበስ፣ ከሌሎች ቢያንስ 6 ጨማ መራቅ፣ ከቤት ዉጭ እንቅስቃሴዎችን መገደብና ሰዉ የበዘበትን ማስወገድ፣ በየግዜዉ እጅ መታጠብ፣ የሲዲሲን የጉዞ መመሪያ መከተል፣ እና ኮቪድ-19 ከየዘዉ ሰዉ ጋ ከተጋለጡ በኋላ የለይቶ ማቆያ መመሪያ መከተልን ያካትታል።

👉 በተደጋጋሚ የሚጠየቁ የCOVID-19 ክትባት ጥያቄዎች

## ስለ የኮቪድ-19 ክትባት የበለጠ ለማዋቅ

- Data dashboard: Summary of COVID vaccination among King County residents
- የዋሽንግተን ስቴት ጤና ክፍል ኮቪድ-19 ክትባት ድህረ-ገጽ
- ሲዲሲ ኮቪድ-19 ክትባቶች ድህረ-ገጽ
- ሲዲሲ ስለ ክትባት ዕቅድ ማዋቅ ያለብን 8 ነገሮች

**Link/share our site at www.kingcounty.gov/covid/vaccine/amharic**

Last Updated January 13, 2021